THE FREEDOM FUND

# የቤት ውስጥ ግርድና ስርጭት በልጅ የቤት ውስጥ ሰራተኞች በአዲስአበባ፣ ኢትዮጵያ

## ማጠቃለያ

ጥቅምት 2022ኢ.ም

ፖፕሌሽን ካውንስል


Annabel Erulkar PhD, Lemi Negeri, Eyasu Hailu
Population Council




POPULATION COUNCIL
Ideas. Evidence. Impact.

DEPARTMENT OF STATE
UNITED STATES OF AMERICA

# ማጠቃለያ

በዓለም አቀፉ የሠራተኛ ድርጅት መሰረት ፣ በዓለም ዙሪያ 17.2 ሚሊዮን የሚደርሱ ወጣት የቤት ሠራተኞች እንደሚኖሩ የሚገመት ሲሆን ፤ ከነዚህም ውስጥ አብዛኞቹ ሴት ወጣቶች ናቸዉ (ILO, 2013; ILO, n.d):: ምንም እንኳን ቁጥራቸው ከፍተኛ ቢሆንም፣ በእነዚህ ትኩረት ባልተሰጣቸው አካላት ዙርያ የተሰሩ ጥናቶች በጣም አናሳ ናቸው። የተሰሩትም ዉስን ጥናቶች የሚያጠነጥኑት በግርድፉ በቤት ዉስጥ ሰራተኞች ላይ ነዉ፡፡ ከልጅ የቤት ውስጥ ሰራተኛ ጋር በተያያዘ ያለው የመረጃ እጥረት ስለ ሴት ልጆች ሊኖረን የሚገባውን ግንዛቤ የሚገድብ፥ የአውድ አግባብነት ያለው ፖሊሲ እና ፕሮግራም ቀረፃ እና ትግበራን በተመለከተ ሊወሰዱ የሚገባቸውን እርምጃዎችን የሚያደናቅፍ ነው ሊባል ይችላል፡፡ ይህ ጥናት፣ በሴቶች የቤት ዉስጥ ሰራተኞች ላይ ከተሰሩ ውስን መጠነ ሰፊ ጥናቶች መካከል አንዱ ሲሆን፤ ጥናቱ ወጣት የቤት ሰራተኞች ያሉበትን ሁኔታ፥ ስርጭቱን፥ ወደ የቤት ዉስጥ ስራ የመግባትን ሂደት፣ በስራዉ ላይ ያላቸዉን ልምድ፣ ከህገ-ወጥ የሰዎች ዝዉዉር አንፃር ያለበትን ደረጃ፣ አደገኛ የቤት-ዉስጥ ሥራዎች እና ህገ-ወጥ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛን ይዳስሳል፡፡

ይህ ጥናት ቅይጥ የምርምር ስልቶችን በመከተል የተሰራና ሰፋ ያለ ናሙናን በመውሰድ  ማህበረሰብ አቀፍ ሆኖ ወጣት  ሴት የቤት ሰራተኞችን ማእከል ያደረገ ገላጭ ስልትን(qualitative method) እና፣ ጥልቅ ቃለ-መጠይቅን ከተወሰኑ ሴት ልጃገረዶች ጋር በማከናወን የተሰራ ነው፡፡ ጥናቱ የተካሄደዉ በአዲስ አበባ ኢትዮጵያ በሚገኙ ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው አካባቢዎች ሲሆን በተለይም በጉዳዩ ላይ ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች፤ እና ባለድርሻ አካላት እገዛልጅ የቤት ዉስጥ ወጣ የቤት ሰራተኞች በብዛት በሚገኙባቸው አካባቢዎች ላይ ነው። ከዚህ ቀደም ራሳቸውን እንደ ቤት ሰራተኛ በሚያዩ ሴቶች ላይ ከተደረጉ ጥናቶች በተለየ መልኩ ይህ ጥናት ወጣት የቤት ሰራተኞች ሰራተኛ መሆናቸውን ከመለየት አንፃር ያለውን አስቸጋሪ ሁኔታ በተለይም የሩቅ ቤተሰብ አባላት የሆኑ ወይም እንደማደጎ የሚታሰቡ ልጆችን እንደ ልጅ የቤት ውስጥ ሰራተኛ ከማየት አንፃር ያለውን ሁኔታ ከግምት አስገብቷል፡፡ ፡፡ ስለዚህም፣ ለዚህ ጥናት “ወጣት የቤት ሠራተኞች” ማለት እራሳቸውን እንደ ቤት ሠራተኛ የሚያዩትን እንዲሁም በሳምንት ከ14 ሰዓታት በላይ የቤት ውስጥ ሥራ የሚሰሩ እና ከአባትና ከእናታቸው ጋር አብረው የማይኖሩትን ያጠቃልላል። እነኚህ ሁለተኛ ላይ የተገለፁትና ራሳቸውን እንደ ቤት ሰራተኛ ባያዩም በዚህ ጥናት ውስጥ የተካተቱበት ምክንያት ለአሰሪዎቻቸዉ የሩቅ ቤተሰብ አባላት በመሆናቸውና በማደጎ ስም ቢኖሩም ነገር ግን እንደ ቤት ሰራተኛ የሚታሰቡ በመሆናቸዉ ነዉ፡፡ በዚህ ጥናት ዉስጥ ልጅ የቤት ዉስጥ ሰራተኛ የስራ ሰዓት፣ በሳምንት 14  ሰአት ተደርጎ እንደ መነሻ የተወሰደበት ምክንያት ይህ ትርጉም ከILO የስራ ትርጉም “ከቀላል ስራ” ወይም የቤት ውስጥ ስራዎች ጋር የሚጣጣም በመሆኑ ነዉ (ILO, 2013)፡፡ በኢትዮጵያ ህግ መሰረት፣ ልጆች ማለት እድሜያቸው ከ18 አመት በታች የሆኑትን ማለት ቢሆንም በዚህ ጥናት ዉስጥ ራሳቸዉን 18 አመት ነን ብለው ያረጋገጡት መላሾችም ተካተዋል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት በጥናቱ ዉስጥ የተካተቱት የጥናቱ መላሾች ከእድሜ ጋር በተገናኘ ከፍተኛ መሳሳትና ግምት ላይ የተመሰረተ ምላሽ እንዳለ በመገመት ነው።

ይህ ጥናት በተካሄደባቸው ቦታዎች እና ከቤተሰብ በተሰበሰበዉ መረጃ መሰረት እድሜያቸው ከ12 እስከ 17 አመት ከሚሆኑ የቤት ዉስጥ ሰራተኞች 37 በመቶ የሚሆኑት ወጣት የቤት ዉስጥ ሰራተኞች መሆናቸዉን ያሳያል። ይህም ቀደም ሲል በኢትዮጵያውያን ወጣቶች ላይ ከተደረጉ የጥናት ውጤቶች ጋር ተመሳሳይ ነው (Erulkar et. Al., 2010)። ራሳቸዉን እንደ የቤት ዉስጥ ሰራተኛ የገለፁትና የዕለት ተዕለት ተግባራቸው እንደ ቤት ሰራተኛ የሚያሰቆጥራቸው ሁለት ቡድኖች የተለያየ መገለጫዎች እና ልምዶች አሏቸዉ፡፡ ራሳቸዉን እንደ የቤት ዉስጥ ሰራተኛ የማይቆጥሩ ነገር ግን የሩቅ ቤተሰብ አባል የሆኑ ሴት ልጆች ወደዚህ ሕይወጥ የሚገቡት በለጋ እድሜያቸው ሲሆን ብዙውን ግዜም ወላጅ አልባ ናቸው።  እራሳቸዉን እንደ ቤት ሰራተኛ ከሚለዩት አንፃርም ጥቂት የተሻለ ኑሮ ሊኖሩ ይችላሉ። ከነዚህም ውስጥ ለምሳሌ የተሻለ የመማር እድል እና በተነፃፃሪነት አነስተኛ የስራ ሰአት ሊጠቀሱ ይችላሉ። ሆኖም ግን ፣ ሁለቱም ወገኖች ለብዙ ሰዓታት የቤት ዉስጥ ስራን እንደሚሰሩ ይህ ጥናት ያመለክታል፡፡ በተጨማሪ እራሳቸዉን እንደ የቤት ዉስጥ ሰራተኛ አድርገዉ የማይቆጥሩ ወጣት ሴቶች ለጉልበት ስራቸዉ የገንዘብ ክፍያ የማግኘት እድላቸዉ በጣም ዝቅተኛ ነዉ፡፡ እራሳቸዉን እንደ ቤት ሰራተኛ አድርገዉ የለዩት ልጃገረዶች ስራን ለረጅም ሰዓት እንደሚሰሩ፣ የጉልበት ብዝበዛ እና ጥቃቶች እንደሚደርስባቸዉ የዚህ ጥናት ዉጤት ያሳያል፡፡ በተጨማሪ፣ እነኝህ ሰራተኞች ለአደገኛ የቤት ዉስጥ ስራዎችና ለህገወጥ የሰዎች ዝውውር ተጋላጭ መሆናቸዉን ይህ ሪፖርት ይገልፃል፡፡

ይህ ጥናት እንደሚያመለክተዉ አብዛኞቹ ሴት ወጣት የቤት ዉስጥ ሰራተኞች ከድሃ ቤተሰብ እና ከተለያዩ ቦታዎች ተሰደዉ የመጡ ናቸዉ፡፡ እነኚህ ሴት ልጆች በትምህርታቸዉ ያልገፋ እና የመደበኛ ትምህርትን ለአምስት አመት ብቻ የተከታተሉ ሲሆን ማንበብ የሚችሉት 62 በመቶ የሚሆኑ ብቻ ነዉ፡፡ በዚህ ጥናት ዉስጥ ወጣት የቤት ሰራተኛን አስመልክቶ የተገኘው አስገራሚ ግኝት ረጅም ሰዓታት በስራ መጠመዳቸዉ ነዉ፡፡ በአማካይ በሳምንት 55 ሰዓታት ይሰራሉ (እራሳቸዉን እንደ የቤት ዉስጥ ሰራተኛ የቆጠሩ ሴቶች - በሳምንት 61 ሰዓታት የሚሰሩ ሲሆን እራሳቸዉን እንደ የቤት ዉስጥ ሰራተኛ ያልቆጠሩ ሴቶች - በሳምንት 49 ሰዓታት ይሰራሉ)፡ ፡ በተጨማሪ 40 በመቶ የሚሆኑ የቤት ዉስጥ ሰራተኛ የሆኑት ሴት ልጆች የእረፍት ቀን የላቸዉም፡፡ እንዲሁም 27 በመቶ የሚሆኑት

ደግሞ በህዝብ በዓላት ቀን እረፍት አይሰጣቸዉም፡፡ እንዲሁም 29 በመቶ የሚሆኑት በጣም በማለዳ ስራ የሚጀምሩ ሲሆን 9 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ በምሽት ጭምር የሚሰሩ ናቸዉ፡፡ እነኚህ ተግባራት የኢትዮጵያ ሕግን እና የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅን የሚፃረሩ ናቸዉ፡፡ እንዲህም ሆኖ፣ ለሴቶቹ ክፍያ ላይከፈላቸው ይችላል፤ ከተከፈልቸውም በጣም አነስተኛ ነዉ። ጥናቱ እንደሚያመለክተዉ፣ 52 በመቶ የሚሆኑ ሴት ልጆች በተለይም እራሳቸዉን እንደ የቤት ዉስጥ ሰራተኛ የማይቆጥሩት የሩቅ ቤተሰብ የሆኑት ሴት ልጆች ክፍያ አይከፈላቸውም፡፡ የሚከፈላቸዉ ደግሞ የሚያገኙት በአማካይ በወር $24(1200 ብር አካባቢ) ነው፡፡ በተጨማሪም እድሜያቸዉ ከ12 እስከ 14 የሆኑ ሴት ልጆች ክፍያ ከሌሎች አንፃር በጣም ዝቅተኛ ሲሆን፣ በወር በአማካኝ $17.5(945 ብር አካባቢ) ይከፈላቸዋል፡፡ ከሚከፈላቸዉ ሴቶች ዉስጥ 27 በመቶ የሚሆኑት የወር ደመወዛቸው የሚቀመጠዉ አሰሪዎቻቸዉ ጋር ነዉ። ጥልቅ ቃለ- መጠይቅ ዉስጥ የተሳተፉ ሴቶች እንደገለጹት አሰሪዎቻቸዉ ጋር የተጠራቀመዉ የወር ደመወዛቸዉ ጭራሹኑ እንዳልተከፈላቸዉ ይናገራሉ፡፡ ከሚከፈላቸዉ ሴት ልጆች መካከል 5 በመቶ የሚሆኑትና በተለይም በዕሜያቸው በጣም ልጆች የሆኑት የወር ደመወዛቸው የሚሰጠዉ ሌላ አካባቢ ለሚኖሩ ቤተሰቦቻቸዉ ሲሆን ፤ በተለይም 14 በመቶ የሚሆኑት እድሜያቸው ከ12 እስከ 14 ያሉ ሴት የቤት ሰራተኞች ክፍያቸው ለቤተሰቦቻቸዉ ይሰጣል፡፡

ጥቂት ሴት ልጆች ከወላጅ ቤተሰቦቻቸው የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኙ ሲሆኑ፣ ብዙ ቁጥር ያላቸው ልጅ የቤት ዉስጥ ሰራተኞች አብዛኛውን ጊዜ በገጠር ለሚገኙ ቤተሰቦቻቸው ድጋፍ ይልካሉ። እራሳቸዉን እንደ የቤት ዉስጥ ሰራተኛ ከለዩት ሴት ልጆች 67 በመቶ የሚሆኑት ደመወዛቸዉን የሚቆጥቡ ሲሆን፣ 51 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ ደመወዛቸዉን ለቤተሰቦቻቸዉ ይልካሉ፡፡
ይህ ጥናት ብዙ ሴት ልጆች ላይ አካላዊ እና ወሲባዊ አሉታዊ ጥቃቶች እንደሚደርስባቸዉ ያመላከተ ሲሆን ይህም ቀደም ሲል በኢትዮጵያውያን ወጣቶች ላይ ከተደረጉ ጥናቶች ጋር ተመሳሳይ ነው (Erulkar et. Al., 2017)። ይህም አሰሪዎቻቸዉ የመኝታ እና የምግብ አገልግሎት ሰጥተው ክፍያቸዉን ስለሚይዙባቸዉ ሊሆን ይችላል። ከዚህ የተነሳ፣ ልጅ የቤት ዉስጥ ሰራተኞች በአሰሪዎቸቻቸዉ ላይ ጥገኛ ስለሚሆኑ፣ አሉታዊ ንግግር ለመናገር አይደፍሩም፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ጥናት ዉስጥ አሉታዊ ሁኔታዎች መኖራቸውን ማመሳከር ከተቻለባቸው መንገዶች መካከል ከአሁን አሠሪዎቻቸዉ ጋር ሲነጻጸር በቀድሞ አሠሪዎቻቸዉ የተፈጸሙባቸዉን ጥቃቶች አቀራረብ የተዛባ መሆኑ፤ የጥቃት ክፍያን መከልከልና ሙሉ በሙሉ አለመከፈል ተብራርተው የቀረቡት ከዳሰሳው ይልቅ ጥልቅ-ቃለመጠይቁ ላይ መሆኑ ማሳያዎች ናቸው። በተጨማሪም፣ የጥናት ዉጤቶችን በምናመሳክርበት ወቅት በዚህ ጥናት ዉስጥ የተካተቱት ሴቶች አሰሪዎቻችን ይበቀሉናል ወይም ስራ አናጣለን በሚል ስጋት አሉታዊ ገጠመኞቻቸዉን ላይገልፁ እንደሚችሉ የቀድሞ ሴት የቤት ሰራተኞች አጽንዎት ሰጥተው ገልፀዋል፡፡

በአጠቃላይ፣ በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት (በU.S. Department of State (2020)) በተቀመጠዉ አመላካች መስፈርት መሰረት፣ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት (52 በመቶ) ሴት ልጆች ለህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባ ሆነዋል (እራሳቸዉን እንደ የቤት ዉስጥ ሰራተኛ የቆጠሩ ሴቶች - 68 በመቶ ሲሆኑ እራሳቸዉን እንደ የቤት ዉስጥ ሰራተኛ ያልቆጠሩ ሴቶች - 35 በመቶ ናቸዉ)፡ ፡ በኢትዮጵያ የሠራተኛ ሕግ ድንጋጌ መሠረት ከ12 እስከ 14 አመት የሆኑት ሴት ልጆች በሙሉ ስራ ላይ የተሰማሩት በህገ-ወጥ መንገድ ሲሆን 87 በመቶ የሚሆኑ እድሜያቸው ከ15 እስከ 17 አመት የሆኑ ሴት ልጆች ደግሞ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ (በተለይም ያለ እረፍት ቀኑን ሙሉ እንዲሰሩ መደረግ) ይፈፀምባቸዋል፡፡

ጥናቱ መከላከል፣ ጥበቃ እና የህግ ከለላን ከመስጠት አንጻር የሚከተሉትን ምክረ ሀሳቦችን ሰጥቷል፤

**መከላከል (Prevension)**

- የአለም አቀፍ የሰራተኛ ድርጅት ኮንቬንሽን 189ን ማፅደቅ ፤ የቤት ዉስጥ ሥራን በሠራተኛ ሕግ ዉስጥ ማካተት (Ratification and Incorporation of ILO Resolution Convention 189)፤
- ልጅ የቤት ዉስጥ ሰራተኞችን በማማከር፣ በመወከል እና ድምፅ በመሆን ጉዳዮቻቸዉ ወደፊት በሚወጡ ፖሊሲዎች እና የሕግ ዉሳኔዎች ዉስጥ እንዲካተት ማድረግ እና ማረጋገጥ፤
- የአካባቢ መዋቅሮችን ለምሳሌ እድሮችን፣ የሀይማኖት አባቶችን፣ የቀበሌ እና የወረዳ መዋቅሮችን በመጠቀምና የስምምነት ውል፤ ለሞዴል አሰሪዎች እዉቅና መስጠትና የመሳሰሉትን ስልቶች በመተግበር በወጣት የቤት ሰራተኞች ላይ የሚደርስን ጥቃት መከላከል።

**ከለላ (Protection)**

- ስደትን እና ወደ ቤት ዉስጥ ስራ መግባትን ለሚያስቡ ሴት ልጆች እና ቤተሰቦች በቂ እና አስተማማኝ መረጃ መስጠት፤
- በመንግስትና መንግስታዊ ባልሆኑ እንዲሁም በማህበራዊ ተቀማት መካከል ያለውን ቅንጅች በማሳለጥ የመለየት፥ የቅብብሎሽ፥ የመጠለያ እና የክትትል ስራን አጠናክሮ መቀጠል።
- ወጣት የቤት ሰራተኞች ላይ የሚደርሰዉን መገለል እንዲቆም ምቹ የሆነ ሁኔታን በመፍጠር በራሳቸው የመተማመን ችሎታቸዉ እንዲጨምር፣ ክህሎታቸው እና ማህበራዊ እሴታቸው እንዲያድግ ፤ በስራ ላይ ያሉትን ህጎችና ማእቀፎቻቸው እንዲገነዘቡ ግንዛቤ ማስጨበጥ እና ከሚገባቸው አገልግሎቶች ጋር ማገናኘት።
- መሰረታዊ የትምህርት አማራጮች ለምሳሌ የህይወት ክህሎት ስልጠና፣ ገንዘብ አያያዝና አጠቃቀም የመሳሰሉትን ለልጅ የቤት ዉስጥ ሰራተኞች ማዘጋጀት እና መስጠት፤

**የክስ ሂደት (Prosecution)**

- ሁሉም የሕግ አስከባሪ አካላት (ፖሊስ፣ አቃቤ ህግ እና ዳኞች) የኢትዮጵያ የአሰሪና ሰራተኛ ህግ፣ ህገ-መንግስት እና ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ መከበሩን ማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ አቅማቸዉን ማጎልበት
- የሕግ ጥበቃውን በማጠናከር ጥቃት በማድረስ፣ በጉልበት ብዝበዛና የህገወጥ የሰው ዝውውር ለሚጠረጠሩ የጥቆማ፤ ምርመራና የፍርድ ቤት ሂደቶችን ለልጆች ምቹ ማድረግ።

ፍሪደም ፈንድ ዘመናዊ ባርነትን ለማጥፋት በአለም አቀፍ ደረጃ የሚደረገዉን እንቅስቃሴ የሚመራ ድርጅት ነዉ፡፡ ዘመናዊ ባርነት በጣም የተስፋፋባቸው አገሮችን እና ዘርፎችን በመለየት በጣም ውጤታማ የሆኑት ግንባር ቀደም ጥረቶችን በመለየት ድጋፍ እናደርጋለን።

ባለራዕይ ከሆኑ ባለሀብቶች፣ መንግስታት፣ ፀረ-ባርነት ድርጅቶች እና ለብዝበዛ ለተጋለጡት አካላት ጋር በመተባበር፣ ባርነት እንዲቀጥል እና እንድስፋፋ የሚያደርጉትን ስርዓቶችን እንታገላለን፡ ፡ ከእነኚህ ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመስራት፣ ተጋላጭ ህዝቦችን እንጠብቃለን፣ በባርነት የተያዙትን ነፃ እናወጣለን ወደ ቤተሰቦቻቸዉ እና ማህበረሰቦቻቸዉ እንመልሳቸዋለን፡፡ እንዲሁም ለወንጀሉ ተጠያ ቂየሚሆኑትን ለህግ እንዲቀርቡ እናደርጋለን፡፡


**The Freedom Fund**
**(Ethiopia Country Office)**
Mayswi Building 7th Floor
Ethio-China Ave
Addis Ababa
Ethiopia
+251 (0) 976 - 80 0506

**The Freedom Fund**
**(UK)**
Lighterman House
30 Wharfdale Road
London, N1 9RY
UK
+44 20 3777 2200

**The Freedom Fund**
**(US)**
315 Flatbush Avenue
#406
Brooklyn, NY 11217
USA
+1 929 224 2448

**Population Council**
One Dag Hammarskjold Plaza
New York, NY 10017
United States
+1 212 339 0500

**Population Council**
Heritage Plaza, 4th Floor
Cameroon Street
Addis Ababa, Ethiopia
+251 (0) 116-631712

www.freedomfund.org
info@freedomfund.org
@Freedom_Fund



The Freedom Fund is a United States 501(c)(3) public charity (EIN number 30-0805768).
The Freedom Fund UK is a company limited by guarantee registered in England and Wales (company number 08926428) and a registered UK charity (registration number 1158838).